በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ
# ቤተ ክርስቲን

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሰኔ ፩ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

- አንዳንዶች ኦርቶዶክሳዊ እምነትንና አምልኮትን ‹‹ጎታች፣ ደረቅ፣ እንዲሁም መራር›› አድርገው ተገቢ ባልሆነ መንገድ ተረድተውታል፡፡
- **ኦርቶዶክሳዊነትን ለመረዳት ወደ ምንጩ ተመልሰን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምንድር ናት? ዋና ዋና መገለጫዎችዋስ ምንድር ናቸው? የሚሉ ነጥቦች እንደሚከተለው እንመልከታቸው፡፡**
- ኦርቶዶክሳዊነት በጉም ውስጥ የሚመራ ሳይሆን እውነተኛና ተገልጦ የሚታይ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ነው፡፡
- ከሁሉ በፊት ቤተ ክርስቲያን ምንድር ናት? በሕይወታችንስ ድርሻዋ ምንድር ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን አስቀድመን መጠየቅ ያስፈልገናል፡፡
- እንደምናውቀው ቤተ ክርስቲያን ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ሕይወትነትና ብርሃንነት በገባልን ቃልኪዳኑና ለደቀ መዛሙርቱ ባስተማራት እውነተኛ ትምህርት ተጠብቀን እንኖርባት ዘንድ የተሰጠችን ስጦታ ናት፡፡
- ይህ ትምህርቱም ሆነ ሕይወቱ በዚህችው ቤተ ክርስቲያን የተነሳ ሳይጠፋ በመካከላችን ይኖራል፡፡
- ቤተ ክርስቲያን ራስ ወደ ሆነው ወደ አምላካችን የምታቀርበን የክርስቶስ አካል ስለሆነች በሥጋ ዓይናችን ከምናየው ከሕንጻው በላይ ሰፊና ታላቅ ናት፡፡
- ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት የነበራትን መልክ እንዲሁም ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን የተረዱበትን ሁኔታ መረዳት የቤተ ክርስቲያንን መላ ሁኔታ በአግባብ ለማወቅ ያገለግላል፡፡ ይህንም ሁኔታ በግልጥ የሚያመለክተን መደገፊያችንም መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

- አንዳንድ ሰዎች ስለ ኦርቶዶክሳዊነት የተሳሳተ ግንዛቤ ጨብጠዋል፡፡ መሠረታችን መጽሐፍ ቅዱስ አይመስላቸውም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የቤተ ክርስቲያናችን መሠረትና ማዕዘን ነው፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እምነትም ሆነ ስለ ትውፊት እንዲሁም ስለ ባሕላችን ያሉን ነገሮች መሠረት ነው፡፡ *ካል ተሰ 2፡15፣ ኤር 6፡16፣ ዕብ 11፡፡*
- ስለ ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ‹‹በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቊረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር፡፡›› *የሐዋ 2፡30-43፡፡* እንደ ተባለው ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን በትምህርተ ሃይማኖትዋ፣ በኅብረትና በአንድነት፣ በጸሎትና እንጀራንም አብሮ በመቁረስ (በአንድነት ማዕድ) ተለይታ የምትታወቅ ነበረች፡፡ ይህችው ቤተ ክርስቲያን ትናንት ነበረች፣ ዛሬም አለች ወደፊትም ትኖራለች፡፡
- ጌታችን እኛን ያስተምሩን ዘንድ ለሐዋርያቱ ያስተማረው የሐዋርያት ትምህርተ ሃይማኖት ነው፡፡ ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረትና አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ነው፡፡
- አንድ መሆንን አስመልክቶ ቅዱስ ጳውሎስ *ገላ 3፡28፡፡* እንደጻፈው ሁላችን የአንዱ የክርስቶስ አንድ አካላት እንደሆንን ተገልጦልናል፡፡
- የክርስትናችን ማዕከሉ በጌታችን በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምነን በአንድነት መቆም ነው፡፡

# <u>ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን</u>

- ኅብረታችንንም በቅዳሴውም ሆነ በሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በአንድነት በማገልገልና በመሳተፍ ልንገልጽ እንችላለን፡፡ *<u>የሐዋ 2፡፡</u>*
- በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር በአንድነት የምናደርጋቸው ማኅበራዊ ግኑኙነቶችም (ሽምግልናው፣ ስለበጎ መመካከሩ፣...) ሳይቀሩ አንድነታችንንና ኅብረታችንን የሚገልጡ ናቸው፡፡ *<u>ቀዳ ጴጥ 5፡5፡፡</u>*
- በቅዱስ ቊርባን በአንድነት ከመሳተፋችን ቀጥሎ በሰንበቴው፣ በዝክሩ፣ በጽዋው ... በአንድነት የምንቆርሰውም ማዕድ ሌላው መገለጫችን ነው፡፡ *<u>ቀዳ ቆሮ 11፡፡</u>*
- በተጨማሪም በግልም ሆነ በአንድነት በሥርዓት የምንጸልየውም ጸሎትም ሌላው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያዊትነት መገለጫ ነው፡፡ *<u>የሐዋ 10፡4፡፡</u>*
- ኦርቶዶክሳዊቱ ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያቱ ትምህርተ ሃይማኖት፣ አንድነታቸው (ኅብረታቸው)፣ ጸሎታቸውና በአንድነትም የተሳተፉት ማዕድ የሚገኝባት ናት፡፡
- በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን አምላካችን ክርስቶስ ራስዋ የሆነች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበረች፡፡ ይህችም ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ መንበሮች የነበሯት ብትሆንም ከሐድያን መናፍቃንን ለመቃወም እንደዛሬው በአንድነት የሚቆሙ አባቶች የሚገኙባት ነበረች፡፡
- በሦስቱም (ኒቂያ፣ ቁስጥንጥንያ፣ ኤፌሶን) አንዲቱ ቤተ ክርስቲያን እንደ አንድ አካል በመሆን መናፍቃንን ረታለች፡፡
- በማስከተልም ካቶሊኮች፣ ፕሮቴስታንቶቹ፣... እየተለዩ የራሳቸው አዲስ መንገድ ጀምረዋል፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

- ኦርቶዶክሳዊነት ከእግዚአብሔር ጋር ባለን እውነተኛ ግኑኝነት ላይ የተመሠረተ ነው።
- መናፍቅ የነበረ ሰው ንስሐ ገብቶና ተምሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመመለስ ወስኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ አስቀድሞ ለማየት የቻለው የቤተ ክርስቲያናችንን ‹‹ደወልና የዕጣኑን መዓዛ››፣ ዲያቆናቱን፣ ወዘተ ነበር።
- ኦርቶዶክሳዊነት ግን በአፍአ ከምናያቸው ከእነዚህ ነገሮች የበለጠ ነው። የኦርቶክሳዊነት መገለጫዎች በውጭ ከሚታዩን ነገሮች ይልቅ በውስጥ እጅግ ጠልቀው የሚገኙ ናቸው።
- ቁምነገሩን ወደ ምናገኝበት ወደ ጥልቁ ከገባን ውጫዊውን ገጽታና ገላጮቹን ነገሮች ሁሉ በሚገባቸው ክብርና በሚጠበቅብንም የመረዳት መጠን ማየት እንችላለን።
- *ለመሆኑ እነዚህ የኦርቶዶክሳዊነት መገለጫዎች ምንድር ናቸው?*
- **የመጀመሪያው ኦርቶዶክሳዊነት በጽኑእ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው።**
- የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርቶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። *ኤፌ 2፡20።*
- የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓቶች እንዲሁም ጸሎቱ፣ ቅዳሴው፣ ወዘተ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።
- ኦርቶዶክሳውያን እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስፈላጊ፣ ልዩ ትኩረትም የምንሰጠውና ትርጉምም ያለው መሆኑን እናምናለን። *ሉቃ 24፡27፣ የሐዋ 17፡1-4።*
- ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት አንዱን በማሳነስ ሌላውንም በመግደፍ የምናምነው ወይም የማናምነው እያልን ልዩነት ወይም ምርጫ አናደርግም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ሁሉን እናምናለን እንቀበላለን።

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

- *ሁለተኛው ትውፊት ነው፡፡ ካል ተሰ 2፡15፡፡*
- ትውፊቱም ከአባቶቻችን ሐዋርያት ትምህርት የወሰድነው ነው፡፡
- አባቶቻችን መጽሐፍ ቅዱስን ተርጉመው አስረክበውናል፤ ይህም ሐዋርያዊ ቅብብል ወይም ውርስ ነው፡፡ እኛም እነርሱን ተከትለን ተጠቅመንበት ለልጆቻችን እናስረክባለን፡፡
- እያንዳንዳችን ካህናት ክህነት ከማን እንደተቀበልን እናውቃለን፡፡ ክህነቱን የሰጡንም ከማን እንደተቀበሉት ያውቃሉ፡፡ እንዲህም እየቆጠርን ወደ መጀመሪያዎቹ ክህነቱን ወደ ሰጡት ሐዋርያት ከዚያም ወደ ሰጣቸውም ወደ ጌታችን እንደርሳለን፡፡
- የቤተ ክርስቲያናችን ጳጳሳት ክህነታቸው/ሥልታናቸው በመንፈስ ቅዱስ የተረጋገጠላቸው የሐዋርያት ወራሾች ወይም ተረካቢዎች ናቸው፡፡
- ሐዋርያቱም እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በተለያየ ቋንቋ እየተረጎሙ እንዲያስተምሩ በመንፈስ ቅዱስ ተፈቅዶላቸዋል፡፡ ይህም የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ መሠረት ነው፡፡ *የሐዋ 2፡፡*
- ይህችውም ቤተ ክርስቲያን ዛሬም የምትገኘው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ናት፡፡ እያንዳንዳችን በምንኖርባት የዓለም ሁኔታ ቤተ ክርስቲያናችን ትገኛለች፡፡
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክናችን አምልኮው፣ ጸሎቱ... ሁሉ የጠላት ዲያቢሎስን ፈተና ታግሰው በማሸነፍ አባቶቻችን ትተውልን ባለፉት በመልካም መሠረት ላይ የቆመ ነው፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

- ዛሬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክናችን የሚገኘው የምንኩስና ሕይወት በገዳማውያን መጥፋት የተነሳ መዘጋት እንደገጠማቸው በበርካታ የዓለማችን ክፍሎች እንደሚገኙ ገዳማት ዓይነት ገጽታ ያለው አይደለም፡፡
- የቁጥር ጨዋታ ባይሆንም በሀገራችን በርካታ አዳዲስ ገዳማት እየተከፈቱ ነው፡፡ ይህም በቤተ ክርስቲያናችን የተቀበልነው መንፈሳዊነት ማሳያ ነው፡፡
- አንዳንድ ሰዎች ‹‹ቤተ ክርስቲያን ሞታለች›› ይላሉ፡፡ ይህም ሐሰት ነው፡፡ ምክንያቱም የሞተ ነገር ፍሬ አይሰጥም፣ ምርት አያመርትም፣ የሞተ አያስነሳምና፡፡ *ማቴ 7፣ ማቴ 16፡18፡፡*
- ደምጸ አራዊት፣ ጸብአ አጋንንት በሚበረቱባቸው ሞት በከበባቸው ምድረ በዳ በሆኑ የቤተ ክርስቲያናችን ገዳማት የመነኮሳቱ ጸሎት በረሃውን ሕይወት ዘርቶበታል፡፡ *መዝ 95(96)፡12፡፡*
- እነዚህም ከአምልኮቱ፣ ጸሎቱ በተጨማሪ ሕይወት የመላባቸው፣ጸጥተኛነት የነገሰባቸው፣ ክብር የሚገለጥባቸው ውበቶች ናቸው፡፡
- አባቶቻችን በዚሁ መንገድ ከካታኮምብ ጀምሮ እግዚአብሔርን ሲያመልኩት ኖረዋል፡፡ በየሰዓታቱ የምናቀርባቸው ምስጋናዎችም በአራተናው መቶ ክፍለ ዘመን በካታኮምብ ይኖሩ የነበሩ አባቶቻችን ያቀረቡት ምስጋና ነው፡፡
- ውብ የሆኑ፣ ሐሴትን የሚያስገኙ የሕይወት ትርጉም ያላቸውን ሕያዋን የሆኑ የቤተ ክርስቲያናችንን ዜማዎች እስኪ እንመልከታቸው፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክን ከሌሎች ተለይታ ልዩ የሆነችው ስለምንድር ነው? አንዳንዶች እንደሚሉት ስለማንንቀሳቀስ ወይም ከሌሎች ጋር ስለማንቀላቀል ነው?
- አዎ ከሌሎች የምንለየው እውነኛውና ንጹሕ የሆነ ስጦታ ተሰጥቶን/ተረክበን ጠብቀን አስጠብቀን ስለምንሄድ ነው። በነዚህም ስጦታዎች (በዶግማችን ወይም በትምህርተ ሃይማኖታችን በትውፊታችን ወይም በሥርዓታችን) አንደራደርም፤ የመደራደሩ ሥልጣን የእኛ አይደለምና። ራእ 2፡25።
- መኪናዬን ባውሳችሁ ‹‹ይህሀ አናዳጅ የቁስ መኪና ናት›› የወጣት መኪና እናስመስላት ብላችሁ ስፒኒንግ ጎማ፣ ቲንት፣ስፖይለር፣ ጩኸት የሚያሰማ ሞተር/ጭስ ማውጫ …. ልታስደርጉበት ትችላላችሁ? መኪናችሁ ስላልሆነ አታደርጉትም።
- የአባቶቻችንን ትምህርት የተረከብነው ተከትሎን ለሚመጣ ትውልድ ለማስረከብ ነው። እነዚህም ትምህርቶች በጌታችን በአምላካችን የተሰጡንና በመጽሐፍ ቅዱስም የተመዘገቡ ናቸው።
- እንዲህ ተረድተን ካልጠበቅናቸው ማንኛውም ሰው መለወጥ የሌለባቸውን ነገሮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለወጥ የሚያስችለው ዕድል ሊያገኝ ይችላል። ‹‹ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።›› ዕብ 4፡14።
- ቤ/ክ ተገቢ የሆኑ መልእክቶችን ማስተላለፍ በሚያስችላት የዕድገት ሂደት ውስጥ ትገኛለች።
- ጌታችን ሕዝቡን በምሳሌና በቋንቋቸው ያስተምር እንደነበረ እኛም ይህን ትምህርት ቋንቋችሁን፣ ዘመናዊውን ቴክኖሎጂ፣ እንዲሁም ሌሎችንም ጠቃሚ ዕድሎች በመጠቀም በማስተላለፍ ላይ እንገኛለን
- መልእክቱን የምናስተላልፍበት ዘዴ የተሻሻለ ቢሆንም ቃሉን (ፍሬ ነገሩን)፣ ትምህርተ ሃይማኖቱን፣ ሥርዓቱን ግን ግን አንለውጥም የኛ ሥልጣን ስላልሆነ።

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለወጥ የሚገባው ነገር ቢኖር እንኳ የሚለወጠው በጸሎት በቅዱስ ፓትርያርኩና በቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡ እነርሱ ይወያያሉ፣ ይመዝኑታል፣ ይፈትኑታል… ምክንያቱም የሚለወጠው ነገር የሚለወጠው ዛሬ ለምንገኘው ለእኛ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ለምትመጣውም ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ በጥንቃቄ ይፈተሻሉ ይመረመራሉ፡፡
- በአሁኑ ጊዜ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮን አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎችን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን … በተመለከተ በጥልቀት የሚወያዩ ኤጲስ ቆጶሳትና ሊቃነ ጳጳሳት የሚገኙበት ሲኖዶስ አለ፡፡ ተቀባይነት ያገኙ ጉዳዮችም የቤተ ክርስቲያኒቱ ውሳኔ ሆነው ይቆጠራሉ፡፡
- በመካከለኛው ዘመን የተነሱ ካቶሊካውያን ‹‹ፖፑ አይሳሳትም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ነው፣ ድንግል ማርያም ኃይለ አርያማዊት ናት ብለው››፣ ፕሮቴስታንቶችም ክህነት አያስፈልግም፣… ብለው በማስተማር የመጀመሪያውን ትምህርት ትተው እንግዳ ትምህርት አምጥተዋል ተከትለውታልም፡፡
- ካቶሊካውያኑ ‹‹ድንግል ማርያም ኃይለ አርያማዊት ናት›› ሲሉ ፕሮቴስታንቶቹ ደግሞ ‹‹እርስዋ እንደማስተላለፊያ ክርስቶስ በማኅጸንዋ አለፈ - ድንግልና የላትም…›› እያሉ በተለያየ ጽንፍ ቆመው እንግዳ ትምህርቶችን አስተምረዋል፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

- ኦርቶዶክሳዊቱ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ካህናቱ ከእግዚአብሔር የተሰጡን ናቸው። እንደ ሰውነታቸውም ድካም ይኖርባቸዋል ብላ ታምናለች። ለመዳን የሥራን አስፈላጊነት፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምንም ድንግል በክልኤ መሆን አማላጅነትና ክብር ከቀድሞ ጀምሮ የነበረውን ትምህርት ሳትለውጥ ኦርቶዶክሳዊቱ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠብቃ ትገኛለች።
- አንዳንዶች ኦርቶዶክሳዊነት የሚለወጥ ትምህርት ስለሌለው ‹‹አሰልቺ›› ነው፣ ‹‹አክራሪነት›› ነው ይሉታል። የፈጣሪአችንን ቃል ለማስተላለፍ አዎ ‹‹አክራሪዎች›› ነን፤ ቃሉን መናገርን አስመልክቶ ከተሰጠን የምንለውጠው ስለሌለን። ከመጀመሪያ ጀምሮ የተሰጠንን በመጠበቃችን ልዩ ነን፤ ከአምላካችን የተሰጠን አደራ ይኸው ስለሆነ።
- እኛ ትምህርትዋ በአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ተጠብቆ የኖረ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች፣ ክብርና በረከት ያገኘንም ክርስቲያኖች ነን።
- እኛ ለ2000 ዓመታት ያህል ፈተናውን ታግሳ ዛሬም በዓለም ላይ እጅግ በመስፋፋትና በማብብ ላይ የምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርቲያን ልጆች ነን። በቤተ ክርስቲያናችንም ባገኘነው በዚህ ማንነታችን መኩራት ይገባናል። ኩራታችንም መንፈሳዊ ኩራት እንጂ ዓለማዊ አይደለም።

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

- ስለ ሃይማኖታችን እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርቲያን ሃይማኖታችንም ጸንተን እንኑርባት እንጂ እንደ ዓለማውያኑ የምንመካ ብቻ አንሁን። እኛ ከማንም የላቅን አይደለንም፣ ነገር ግን ተባርከናል። ችሎታችንንም ሳንቀብር እንጠቀምበት።
- የቤተ ክርስቲያን በመሆናችሁ እርስ በርሳችሁ - ስለ ሊቃነ ጳጳሳቱም፣ ስለ ቀሳውስቱም፣ ስለ ዲያቆናቱም ቤተ ክርስቲያናችንን በቅንነት ስለሚያገለግሉ ሁሉ ለምነገኘው አገልግሎት ተሰጥተውናልና ሌላውን ሁሉ ትተን በጎውን ብቻ እየቆጠርን እናመስግን።
- ቤተ ክርስቲያናችን በጌታችን በአምላካችን የተመሠረተች፣ በአባቶቻችን ተጠብቃ፣ በቅዱሳኑና በሰማዕታቱ ጠንክራ ልንረዳው በምንችለው መልኩ እውነተኛውን የምስራች እስከ ዛሬ ድረስ እያበሠረች የምትገኝ ናት።
- የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆናችሁ ደስ ይበላችሁ።
- በእምነታቸው፣ በጥንካሬአቸውና ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃላቸው ቤተ ክርስቲያንን እንደጠበቁት አባቶች ባለ ሕይወት እንኑር።
- ‹‹የፊተኛውንም እምነታቸውን ስለ ናቁ ይፈረድባቸዋል።›› *ቀዳ ጢሞ 5:12።* እንደተባለ እንዳይደረግብን ከፍርድ ይጠብቀን።
- ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔርና ቤተ ክርስቲያኑ ለሆነች ለቤተ ክርስቲያናችን ይሁን አሜን።

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org